የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን
Ethiopian Agricultural Authority

## ከኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ጋር በመተባበር በየአስራ አምስት ቀኑ የሚታተም

# የተቋሙ የእንስሳት ምርትና ግብዓት ቁጥጥር ውጤታማ ክንውን

የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን፣ የግብርና ቴክኖሎጂ፣አገልግሎቶችን ግብዓቶችና ምርቶችን ጥራት፣ ደህንነት፣ ፍቱንነት፣ ፈዋሽነት፣ ጤናማነትና ቀልጣፋነትን ማረጋገጥን ተልዕኮ ያደረገ ተቋም ነው። መልካም ስም ያለውና፣ ለአካባቢ ጥበቃ ተገቢውን ትኩረት የሚሰጥ የቁጥጥር ተቋምና ሥርዓትን በመገንባትና የግብርና ቁጥጥር ሥራዎችን በመተግበር፣ የግብርና ምርቶችን የሀገር ውስጥና የዓለም ገበያ ተደራሽነትና ተወዳዳሪነትን በማሳደግ ለላቀ ሀገራዊ ጥቅምና የኢኮኖሚ ዕድገት የሚጠበቅበትን አስተዋፅኦ ማበርከት ተጨማሪ ተልዕኮዎቹ ናቸው።

በሁለት ዋና ዋና የቁጥጥር ዘርፎች ማለትም በእጽዋት ቁጥጥር ዘርፍ እና በእንስሳት ቁጥጥር ስር ባሉ ክፍሎቹ የተደራጀና ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣ ተቋም ነው:: በ2018 በጀት ዓመትም የ10 ዓመትና የመካከለኛ ዘመን የግብርና ሴክተር ዕቅድ አካል የሆነውን የግብርና ሬጉላቶሪ ዕቅድ መሠረት በማድረግ ባለፉት ስድስት ወራት ባከናወናቸው ተግባራት አምርቂ ውጤቶችን ማስመዝገብ ችሏል::

ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ በግማሽ ዓመት ውጤታማ ሥራ ከተሠራባቸው ከዋነኛ እቅድ ስትራቴጂክ ግቦችና ክንውኖች መካከልም የእንስሳትና ከእንስሳት ጋር የተገናኙ የግብዓቶች፣ ምርቶች፣ ቴክኖሎጂ እና አገልግሎቶች ቁጥጥር ማጠናከርና ማጎልበት አንደኛው ነው::

### የእንስሳት ምርትና ግብዓት ቁጥጥር

ተቋሙ በእንስሳት ምርትና ግብዓት ቁጥጥር በተለይም የእንስሳት ምርቶችን ጤንነት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ ረገድ ባለፉት ስድስት ውጤታማ ሥራን ሠርቷል:: በኢንስፔክሽን በቅድመና ድህረ እርድ ምርምርና ሌሎች አሰራሮች ጤንነት፣ደህንነትና ጥራቱን የጠበቀ 12ሺ 500 ቶን ሥጋና ተረፈ ሥጋ ምርት ለውጭ ገበያ እንዲቀርብ ለማስቻል፣ አቅዶ በድምሩ በ11ሺ 375 ቶን መከወን ችሏል::

የእንስሳት ምርት ጥራትና ደህንነት በላቦራቶሪ ምርመራ በማረጋገጥ ረገድም ለአብነት ባለፉት ስድስት ወራት በ189 የጥሬ ወተት ናሙናዎች ላይ የአፍላቶክሲን እና የምግብ ንጥረ ነገር ይዘት የፊዚኮ-ኬሚካል ምርመራ እንዲሁም በ204 የእንስሳት ምርት (159 ሥጋ፣ 33 ወተት እና 12 እንቁላል) ናሙናዎች ላይ ደግሞ የማይክሮባዮሎጂ ጥራትና ደህንነት ምርመራ በእቅድ ከተያዘው በላይ ማከናወን ችሏል::

ይሁንና በዚህ ረገድ የተለዩ ውስንነቶች ልዩ የመፍትሄ ትኩረትን የሚሹ ናቸው:: በተለይም በጥሬ ወተት ምርት ናሙናዎች ላይ የተገኘው ከፍተኛ የጥራት ችግር (ያልተፈለገ ቅየጣ)ና የወተት አፍላቶክሲን እንዲሁም በእንስሳት ምርት ወይም ተዋጽኦ ናሙናዎች ምርመራ ላይ የታየው የጎጂ ተዋስያን ብክለትና የጸረ ተዋስያን መድኃኒት በጀርሞች መላመድ ችግር ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ የጤና ስጋት በመሆናቸው በንጽህና አያያዝና በእንስሳት መድኃኒት አጠቃቀምና ቁጥጥር ላይ በትኩረትና በስፋት ሊሰራበት ይገባል።

### ኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶችን በማጎልበት ረገድም ውጤታማ ሥራ መሥራት ችሏል:: በስድስት ወራቱም 316 ሺ የቁም እንስሳትን (ዳልጋ ከብት፣ ግመል፣ በግና ፍየል) በኳራንቲን ጣቢያዎች በማቆየት የጤና ምርመራና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ፣ ለ306 ሺህ 085 እንስሳት የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ወደ ውጭ ሀገር እንዲላኩ አድርጓል።

በስድስት ወሩ ውስጥ ጥራቱ፣ ደህንነቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የሚላክ 282ሺ የአንድ ቀን ጫጩትና የለማ እንቁላል ኤክስፖርት ለማድረግ አቅዶ የነበረ ቢሆንም፣ ምንም ዓይነት ክንውን አልተመዘገበም። በ6 ወሩ ይከናወናል ተብሎ የታቀደው ኤክስፖርት መጠን ላለመከናወኑም የራሱ ምክንያት አለው:: ይህም የገበያ ፍላጎት በማጣቱ ሳይሆን፣ በሀገር ውስጥ የሚታየውን ከፍተኛ ፍላጎት ለማሟላትና የሀገር ውስጥ ገበያን ለማረጋጋት ሲባል በግብርና ሚኒስቴር እና በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ውሳኔ ወደ ውጭ የመላክ እቀባ በመጣሉ ነው።

> **የመኖ ምርት ጥራት መጓደል የእንስሳት ምርትና ምርታማነት ይቀንሳል፤ የመኖ ደህንነት ችግር የእንስሳት ጤናና በእንስሳት ምርት ደህንነት ጉድለት በሰው ጤና ላይ አደጋ ያስከትላል:: የእንስሳት አርቢ ዜጎች ያለ አግባብ ተጨማሪ የገንዘብ ኪሳራ እንዲደርስባቸው ያደርጋል**

በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት ጤንነቱና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር የሚገባ 369 ሺ 246 የአንድ ቀን ጫጩትና የለማ እንቁላል ለማስገባት ታቅዶ፣ ለአንድ ሚሊዮን 775 ሺ 681 ምርቶች የኢንስፔክሽንና የቁጥጥር ሥራ በማከናወን ወደ ሀገር እንዲገቡ ተደርጓል። ይህም ከዕቅዱ አንጻር እጅግ የላቀ አፈጻጸም ነው።

ለዚህ አፈጻጸም ከፍተኛ መሆን ዋነኛው ምክንያት "የሌማት ትሩፋት" ሀገራዊ መርሃ-ግብር በዘርፉ ላይ የፈጠረው ከፍተኛ መነቃቃትና በሀገር ውስጥ የታየው ሰፊ የዶሮ እርባታ ፍላጎት ነው። መንግሥት ለዘርፉ የሰጠው ልዩ ትኩረትና የተቀናጀ የሥራ ዕድል ፈጠራ ተግባራት ለግብዓቶቹ ፍላጎት መጨመር አስተዋጽኦ ያደረጉ ሲሆን፣ ተቋሙም የሬጉላቶሪና የቁጥጥር አገልግሎቱን በማቀላጠፍ የምርቶቹን ጤንነትና ጥራት በማረጋገጥ ወደ ሀገር እንዲገቡ አድርጓል።

በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት ጤንነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ 165 የተሻሻለ ዝርያ ያለው ዳልጋ ከብት ለማስገባት ታቅዶ፣ በክንውን 535 ከብቶችን ማስገባት ተችሏል። ይህም ከዕቅዱ አንጻር እጅግ የላቀ አፈጻጸም መመዝገቡን ያሳያል። ይህ ከፍተኛ ስኬት በሀገር ውስጥ ያለውን የወተት ምርታማነት ለማሳደግ የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝ ሲሆን፣ ተቋሙም አስፈላጊውን የጤና ምርመራና የኳራንቲን ቁጥጥር በማድረግ ምርጥ ዝርያ ያላቸው ከብቶች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ አመቻችቷል።

በግማሽ ዓመቱ ለቁም እንስሳት፣ ለእንስሳት ምርቶች እና ለተረፈ ምርቶች ኤክስፖርት ዘርፍ በተሰማሩ 33 ድርጅቶች ላይ የኢንስፔክሽን ሥራ ለማከናወን አቅዶ፣በ37 ተቋማት ላይ ቁጥጥር አድርጓል። ይህም ከዕቅዱ አንጻር ውጤታማ አፈጻጸም ሲሆን፣በተቋማቱ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት የጥራትና የሬጉላቶሪ መስፈርቶችን ማሟላታቸውን በማረጋገጥ የውጭ ንግድ ሂደቱ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን አስችሏል::

ባለፉት ስድስት ወራት በተቀባይ ሀገራት መስፈርት መሠረት ለኤክስፖርት ለተዘጋጁ 80 ሺህ የቁም እንስሳት የደም ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ፣ለ103 ሺህ 123 እንስሳት ምርመራው ተከናውኗል። ይህም ከዕቅዱ አንፃር የላቀ አፈጻጸም የታየበት ተግባር ነው።

በምርመራው ውጤት መሠረት የጤና ችግር የተገኘባቸው 11ሺህ 240 እንስሳት ወደ ውጭ እንዳይላኩ ተለይተው የተቀነሱ ሲሆን፣ይህም በተቀባይ ሀገራት ላይ ሊከሰት ይችል የነበረውን የጤና ስጋትና በሀገሪቱ የውጭ ንግድ ላይ ሊፈጠር ይችል የነበረውን እገዳና መስተጓጎል አስቀድሞ ለመከላከል አስችሏል።

### ጥራት፣ ደህንነቱና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳትመድኃኒት

የተቋሙ የእንስሳት ምርትና ግብዓት ቁጥጥር ዘርፍ ውጤታማ ክንውን በጥራት፣ደህንነቱና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድኃኒት ላይም ተመዝግቧል:: ለአብነትም ጥራት፣ ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ወይም የተመረተ የእንስሳት መድኃኒት ረገድ በ2018 በጀት እስከ 2ኛ ሩብ ዓመት አንድ ሺ 750 ቶን ጥራት፣ ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ወይም ተመርቶ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ ታቅዶ ሁለት ሺህ 195 ቶን የእንስሳት መድኃኒት ጥራቱ፣ ደህንነቱና ፈዋሽነቱ እንዲረጋገጥ ተደርጓል:: አፈጻጸሙም ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት ተገልጋዮች አገልግሎቱን ፈልገው በብዛት በመምጣታቸው ነው::

በኢንስፔክሽን ሥርዓትና በላቦራቶሪ ምርመራ ተረጋግጦ የተመዘገበ የእንስሳት መድኃኒት ረገድም፣ በበጀት ዓመቱ እስከ 2ኛ ሩብ ዓመት 60 የሚሆኑ የእንስሳት መድኃኒቶችን በመገምገም፣ በኢንስፔክሽን ሥርዓትና በላቦራቶሪ ምርመራ በማረጋገጥ ለመመዝገብ ታቅዶ 80 የእንስሳት መድኃኒት እንዲመዘገብ ተደርጓል:: አፈጻጸሙም ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት አሠራሩ ዲጂታላይዝድ ከሆነ በኋላ አምራች ድርጅቶች ከሀገር ውስጥ ባለ ተወካይ በተጨማሪ የምዝገባ ሂደቱን የሚከታተሉት በመሆኑና የተለያዩ የመድኃኒት አማራጮች የመመዝገብ እድል በመፈጠሩ ነው::

በተጨማሪም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በ2018 በጀት እስከ 2ኛ ሩብ ዓመት ለ350 የእንስሳት መድኃኒት አምራች፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር በመስጠት፣ለነባር የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያዎች የሙያ ፈቃድ በማደስ፣ ለአዲስ የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ የሙያ ፈቃድ አገልግሎት በመስጠት፣ በእንስሳት መድኃኒትና ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን በማድረግና ውስንነት የታየባቸው ላይ የተለያዩ ርምጃ ከመውሰድ አንፃር ውጤታማ ሥራዎች መሥራት ችሏል::

### ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መኖ

ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መኖ ማረጋገጥ ሌላው በልዩ ትኩረት ውጤታማ ሥራ የተሠራበት ነው:: ለአብነትም፣ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኙ መኖ አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማትን ከማጎልበት አንጻር፣ በስድስት ወራት ለ398 የመኖ አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ንግድ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመስጠት ታቅዶ ለ326 ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት ተችሏል።

ለወጪ ንግድ ለሚቀርብ የእንስሳት መኖና የመኖ ጥሬ ዕቃ የቅድመ ማስወጫ ፈቃድ 150 ለመስጠት ታቅዶ የተቀባይ ሀገራትን መስፈርት ላሟላ 129 ተሰጥቷል:: በዚህ የመኖ ወጪ ንግድ የቅድመ ማስወጫና በጣቢያዎች የመልቀቂያ ፈቃድ ተሰጥቶ 254 ሺ 52 ነጥብ 5 ቶን የመኖ ጥሬ ዕቃ ወደ ተለያየ ሀገራት የተላከ ሲሆን፤ ከዚህ ወጪ ንግድ 13 ሚሊዮን 468 ሺህ 816 የአሜሪካ ዶላር ተገኝቷል::

ጥራቱና ደህንነቱ ተረጋግጦ የተመረተ የተቀነባበረ መኖ አቅርቦት ረገድም በግማሽ ዓመቱ 150ሺ ቶን የተቀነባበረ መኖ ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ለገበያ እንዲቀርብ ታቅዶ 138 ሺህ 725 ቶን ተመርቷል:: የእንስሳት መኖ ጥራትና ደህንነትን ማረጋገጥ ረገድ ውጤታማ ሥራ መሥራት ቢቻልም በአንዳንድ ምርቶች ላይ ከተቀመጠው የደህንነት ስታንዳርድ በታችና በላይ መሆን፣ በተለይ የአፍላቶክሲንን መጠን ጨምሮ መታየት ተስተውሏል:: ለችግሩ ልዩ ትኩረትና መፍትሄ ሊሰጠው የሚገባ ነው::

የመኖ ምርት ጥራት መጓደል የእንስሳት ምርትና ምርታማነት ይቀንሳል፤ የመኖ ደህንነት ችግር የእንስሳት ጤናና በእንስሳት ምርት ደህንነት ጉድለት በሰው ጤና ላይ አደጋ ያስከትላል:: የእንስሳት አርቢ ዜጎች ያላ አግባብ ተጨማሪ የገንዘብ ኪሳራ እንዲደርስባቸው ያደርጋል:: በመሆኑም የመኖ ምርት ጥራትና ደህንነት እንዲሻሻል ቀጣይነት ያለው ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ የግድ ይላል:: ለዚህም ሁሉም የድርሻውን ኃላፊነት ሊወጣና ከተቃሙ ጋር በቅንጅት ሊሠራ ይገባል::

ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳትና የዕጽዋት ጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ አገልግሎት በመስጠት ረገድ፣ ዓለም አቀፍ የላቦራቶሪ ጥራት ማኔጅመንት ሥርዓት ትግበራ ሥራዎችን አጠናክሮ በማስቀጠል ማዕከሉ ከዚህ በፊት እውቅና ወይም አክሪዲቴሽን ያገኘባቸውን 13 የምርመራ አይነቶችን (በፋርማስውቲካል፣ በኬሚካልና በማይክሮባዮሎጂካል) በማስቀጠል ደረጃውን የጠበቀ የላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ አገልግሎት መስጠት ችሏል:: ይህም ተቋሙን በውጤታማ አፈፃጸም ለማጀብ አቅም በመፍጠር ረገድ ተጨባጭ አቅምን የሚፈጥር ነው::

ባለፉት 6 ወራት ከተከናወኑ አበይት ክንውኖች መካከልም ከተለይ ባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ቅንጅታዊ አሠራሮች የትብብር ስምምነቶች ለክልል ባለድርሻ አካላት የተደረጉ የቴክኒክና የስልጠና ድጋፎች፣ የዳሰሳ ጥናቶች ዋናውን ድርሻ የያዙ ሲሆን፤ በክንውኖቹም የግብርና ሬጉላቶሪ ሥራዎች እንዲጠናከሩ አቅም መፍጠር ችለዋል::

ለአብነትም የስጋና የተረፈ ስጋ ኤክስፖርቱን ለማሳደግ መልካም አጋጣሚዎችና ተግዳሮቶች ዙሪያ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት በቅርበት ተሰርቷል:: ከጆርዳን መንግሥት ጋር በተደረገ ተደጋጋሚ ውይይትና የጆርዳን ሬጉላቶሪ ተቋማት ኃላፊዎች መጥተው የኢትዮጵያ ስጋ ወደ ጆርዳን መላክ ተጀምሯል:: ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር ከእንስሳት ምርት ጥራት፣ ጤንነትና ደህንነት ጋር የተያያዙ አራት ነባር ስታንዳርዶች የመከለስ ሥራ ተሠርቷል::

በአጠቃላይ ባለፉት ስድስት ወራት የባለስልጣኑ አፈጻጸም ውጤታማ ነበር:: ይሁንን ውስንነቶችና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችም ተለይተዋል:: በመሆኑም በቀጣይ ባለፉት ጊዜያት የታዩ ክፍተቶች ላይ ይበልጥ መሥራት የግድ ይላል:: ውጤቶች ማስቀጠል፣ ታቅደው ያልተከናወኑ ተግባራትን መከወን፣ ወጪ ቆጣቢ የሆኑ የአሠራር ዘዴዎችን መጠቀም እንዲሁም ዲጂታላይዜሽንና አውቶሜሽን አሠራሮችን ማጠናከር ልዩ ትኩረት ተሠጥቶ የሚሠራባቸውም ይሆናል::